# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 136 ታህሳስ 14 ቀን 2003 ገጽ 1


የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ

**“የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!:”**

**ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ “እምቢ ለመብቴ!!!” ብቻ ነው**

## በአለም ዙሪያ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ጸረ-ሰቆቃ ጥምረት መሰረቱ

በትግራዩ ገገር ጉጅሌ እስር ቤቶች ውስጥ የሚካሄደውን ሰቆቃ የሚያጋልጥ ሰፊ ሪፖርት ያወጡት አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ላደረጉት ጥሪ ምላሽ በመስጠት፤ በአለም ዙሪያ ያሉ ኢትዮጵያውያን "አለማቀፍ ጸረ-ሰቆቃ ጥምረት" መመስረታቸው ታውቋል።

የጥምረቱ መስራቾች ስለ ጥምረቱ መመስረት ይፋ ባደረጉበት መግለጫ "በአገዛዙ የደህንነት እና የፖሊስ ተቋማት ውስጥ የሚሰሩት ቆራጥ ኢትዮጵያዊያን የወያኔ አገዛዝ በንጹሃን ዜጎች ላይ እየፈጸመ ያለውን ሰቆቃ ለአለም ህዝብ ይፋ ለማድረግ እድል ስላልነበራቸው እኛ በውጭ በስደት ላይ የምንገኝ ወገኖቻቸው ሥራውን እንደምንሰራ በመተማመን መረጃውን ይፋ አድርገዋል" ካለ በኋላ የነርሱን ጥሪ በመቀበል ወያኔ እየፈጸመ የሚገኘውን ሰቆቃ ለአለም አቀፍ ህብረተሰብ ጆሮ በማድረስ እንዲህ አይነት ዘግናኝ ድብደባ በአስቸኳይ እንዲቆም ፤ እስከዛሬ ሰቆቃው ለተፈጸመባቸው ፍትህ ለማስገኘት ጠንክረን ለመስራት በመወሰን ተደራጅተናል ብለዋል።

በተለያዩ አገራት በሚገኙ ኢትዮጵያውያን የተቋቋመው ይህ ጥምረት "ግሎባል አላያንስ አጌነስት ቶርቸር ኢን ኢትዮጵያ" ወይም "አለማቀፍ የጸረ-ሰቆቃ ጥምረት ለኢትዮጵያ" እንደሚባል በትናንትናው ዕለት ይፋ የተደረገው መግለጫ ያመለክታል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የወያኔ ጦር ከሰሞኑ በኦጋዴን ንጹሃን ዜጎች ላይ የጅምላ ጭፍጨፋ አድርሶአል ተባለ

በኦጋዴን የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን አሁንም የትግራዩ ገገር ጉጅሌ የጭካኔ በትር ኢላማ ሆነው መሰንበታቸውን የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር (ኦብነግ) እንደገለጸ ኦል ሄድላይን ኒውስ የተባለ የዜና ድረ-ገጽ ዘግቧል።

የኦብነግ የኢንፎርሜሽን ክፍል ሃላፊ አቶ ሁሴን ሙሃመድ ኑር እንደገለጹት፣ ሃያ ንጹሃን ዜጎች በዘረኛው አገዛዝ ወታደሮች ተጨፍጭፈዋል። ግድያዎቹ የተፈጸሙትም በቆራህሌ፣ በፋርማዶው፣ እና በዲጋህቡር እንደሆነና ወታደሮቹ በርካታ ጎጆ ቤቶችን እንዳቃጠሉም ዘገባው አመልክቷል። አቶ ሁሴን፥ ኦብነግ የወያኔን ወታደሮች ለፈጸሙት ግፍ እንደሚበቀላቸው ገልጸዋል።

የትግራዩ ገገር ጉጅሌ ከጥቂት አመታት በፊት ኦብነግን በማጥፋት ስም ጦሩን ወደ ኦጋዴን ልኮ ከፍተኛ እልቂት እንደፈጸመ የሚታወቅ ሲሆን፤ አለማቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ለጋሽ አገራት በዘረኛው አገዛዝ የእርዳታ ስርቆት ላይ ምርመራ ሊያካሄዱ ነው

በአዲስ አበባ የሚገኙ የለጋሽ አገራት እና ተቋማት ተወካዮች በወያኔ የእርዳታ ስርቆት ላይ ምርመራ ለማድረግ ዝግጅት እያደረጉ ነው ሲል ብሉምበርግ የዜና አገልግሎት ዘግቧል።

ሂውማን ራይትስ ዋች የተባለው አለማቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ቡድን በጥቅምት ወር ባወጣው ሰፊ ሪፖርት፣ የትግራዩ ገገር ቡድን በደሆች ስም ከምእራባውያን የሚሰበሰበውን ገንዘብ ለአፈና ተግባር እያዋለ መሆኑን ዝርዝር ማስረጃ በማሳየት ማጋለጡ ይታወሳል።

"ደቨሎፐመንት አሲስታንስ ግሩፕ" የተባለው እና 26 ለጋሾችን የሚያካትተው ቡድንም በዚህ ሪፖርት ላይ በተዘረዘሩት ክሶች ላይ ምርመራ ለማድረግ ውይይት ሲያካሄድ መቆየቱን ብሉምበርግ ዘግቧል። የአለም ባንክ፣ አይ.ኤም.ኤፍን እና የአሜሪካን መንግስት የሚያካትተው ይህ ቡድን ከዚህ ቀደም ለሂውማን ራይትስ ዋች በሰጠው ምላሽ ከሰብአዊ መብት ተሟጋች ቡድኑ ሪፖርት ጋር አልስማማም ማለቱ አወዛጋቢ ሆኖ መቆየቱ ይታወቃል።

ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ የለጋሽ ቡድኖቹ ሰራተኞች ወያኔ የእርዳታ ገንዘብ ለአፈና እያዋለ እንደሆነ በድብቅ ለሂውማን ራይትስ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በቦሌ አካባቢ በሚገኝ የአፈና ጣቢያ ንጹሃን እንደሚሰቃዩ ታወቀ

የትግራዩ ገገር ጉጅሌ በቦሌ አካባቢ ባቋቋመው የሰቆቃ ጣቢያ በርካታ ንጹሃን እየተሰቃዩ እንደሚገኙ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን በላኩት መረጃ አስታውቀዋል።

ዘረኛው አገዛዝ ባለፉት ሃያ አመታት ውስጥ በርካታ የምስጢር እስር ቤቶችን በአገሪቱ ዙሪያ ከፍቶ ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ ዜጎችን እያፈነ ሲያሰር እንደነበር ሲነገር ቆይቷል። ሰሞኑን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰ መረጃ እንደሚያመለክተው፥ ከነዚህ እስር ቤቶች ውስጥ አንዱ በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ አካባቢ ይገኛል።

ይህ ጣቢያ በብብሔራዊ መረጃ እንደሚመራ እና ትግርኛ ብቻ የሚናገሩ አስራ አንድ ሰራተኞች እንዳሉትም ለማወቅ ተችሏል። እነዚህ ሰራተኞች ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ እና ያለ ፖሊስ መጥሪያ ዜጎችን አፍነው ፊታቸውን በጨርቅ በመሸፈን እና አፋቸውን በፐላስተር በማሸግ፤ ጥቁር መስታወቶች እና ቁጥር 2 ታርጋ ባሏቸው ኮብራ መኪናዎች ወደ እስር ቤቱ እንደሚወስዷቸው መረጃው ያስረዳል።

ወደ አፈና ጣቢያው በደረሱ ግለሰቦች ላይ የተለያዩ የሰቆቃ ተግባራት የሚፈጸሙ ሲሆን፤ የተሰነዘረባቸውን ወንጀል የማይቀበሉት ተገድለው እንደሚቀበሩ እና ያመኑት ወደ ማእከላዊ እስር ቤት እንደሚዘዋወሩ በአገዛዙ የደህንነት ተቋም ውስጥ የሚሰሩ ምንጮች ገልጸዋል። ከሞት ከተረፉት ውስጥ በርካቶች እስካሁን በማእከላዊ እስር ቤት፣ በፌዴራል ማረሚያ ቤት እና በየጦር ካምፖች ውስጥ ሰቆቃ እየተፈጸመባቸው ነው።

ወደዚህ ጣቢያ ተወስደው ለስቃይ ከተዳረጉ ዜጎች ውስጥ ከኬንያ፣ ከጅቡቲ፣ ከሶማሊያ እና ከሱዳን ታፍነው የመጡ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ብዙ እንደሆኑ ከመረጃው ለማወቅ ተችሏል።

## በጋምቤላ የተፈጸመው የዘር ማጥፋት ወንጀል ጉዳይ በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት ፊት መሆኑ ታወቀ

ዘረኛው አገዛዝ ከሰባት አመታት በፊት በጋምቤላ ፈጽሞታል የሚባለው የዘር ማጥፋት ወንጀል ጉዳይ በአለም አቀፍ ወንጀለኛ ፍርድ ቤት ፊት እየታየ መሆኑን ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ግለሰቦች ገልጸዋል።

በዚህ ሳምንት የጭፍጨፋው ሰባተኛ አመት ታውሶ ሰንብቷል። መታሰቢያውን በሚመለከት ከዶ/ር አለማየሁ ገብረማርያም ጋር ውይይት ያደረጉት ኢትዮጵያዊው የሰብአዊ መብት ተሟጋች አቶ ኦባንግ ሜቶ የጋምቤላው ጉዳይ በአለማቀፉ ወንጀለኛ ፍርድ ቤት ፊት እንደሚገኝ ገልጸዋል። የተባበሩት መንግስታት ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ኮሚሽነር ጀኖሳይድ ዋች በተባለው የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት ፕሬዚደንት ዶ/ር ግሬጎሪ እስታንተን የተላከለትን ጥሪም በመቀበልም ጉዳዩን እያጠና ነው ብለዋል።

(ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## የወያኔ "ባለስልጣናት ሆዳቸው አይሞላም" ሲል የሰበታ ከተማ ከንቲባ አወገዘ

በአዲስ አበባ ዳርቻ ላይ የምትገኘው የሰበታ ከተማ ከንቲባ ለወያኔ ባለስልጣናት ከፍተኛ መጠን ያለው የመሬት ይዞታ ቢያከፋፍልም ሆዳቸው የማይሞላ ሆነው እንዳስቸገሩት ለቅርብ ወዳጆቹ ማውጋቱን ለግለሰቡ ቅርብ የሆኑ ሰው ለዘጋቢያችን ገልጸዋል።

የሰበታ ከተማ ከመሬት ጋር በተያያዘ በከፍተኛ ሙስና ውስጥ ተዘፍቀው ከሚገኙት ከተሞች ውስጥ አንዷ እንደሆነች እና በቅርቡም መሃንዲሶችን ጨምሮ በርካታ የከተማዋ የመሬት አስተዳደር ሰራተኞች መታሰራቸውን፤ የመለስ ዜናዊ ሚስት አዜብ መስፍንም እራሷ በስፍራው ተገኝታ የእስሩ ዋና አቀናባሪ እንደበረች ዘግበናል። ይሁን እንጂ፥ መሃንዲሶቹም ሆኑ ሌሎቹ ሰራተኞች በሙሉ እነ አባ ዱላ ገመዳን ጨምሮ ከበርካታ የወያኔ ባለስልጣናት ጋር በመመሳጠር እንደሚሰሩ ከተለያዩ ምንጮች የደረሰን መረጃ አመልክቷል።

ዘጋቢያችን አጠናቅሮ በላከው ዘገባ በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ የሚገኙ የኦሮምያ ክልል ከተሞች የድለላ ተቋሞች እንጂ የመንግስት መስሪያ (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## በዘረኝነት ላይ ወታደራዊ አገዛዝ “በልማት” ተቋማት

በተለምዶ “የልማት ተቋማት” ተብለው በሚጠሩት የኢትዮጵያ ህዝብ ንብረት በሆኑት የመሠረተ ልማት ወይም የቢስነዝ ተቋማት ውስጥ የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ካሰፈነው ዘረኝነት በተጨማሪ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መሠሪ የሆነ ተግባር እየተጠናከረ መጥቷል። ጉጅሌው “ስትራቴጂያዊ” የሚላቸውን ተቋማት እንዲቆጣጠሩ የሚመርጣቸው ሰዎች ከዘረኝነት መስፈርት በተጨማሪ ወታደራዊና የስለላ ልምድ ያላቸው እንዲሆኑ እየተደረገ ነው። በደርግ ጊዜ የአብዛኛዎቹ የሲቪል ኮርፖሬሽኖችና ፋብሪካዎች ማኔጀሮች ወታደራዊ መኮንኖች እንደነበሩ ሁሉ አሁንም የወታደራዊና የጆሮ-ጠቢነት የሥራ ልምድ ያላቸው የትግራይ ገዢ ጉጅሌ የቅርብ የሥጋና የጋብቻ ዘመዶች ለሲቪል ኮርፖሬሽኖች ማኔጀርነት እየታጩ ነው።

ለእንደዚህ ዓይነቱ ዘረኛ “ሚሊታራይዜሽን” ከተጋለጡት ተቋማት ውስጥ የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን ቀዳሚ ተጠቃሽ ነው። ቴሌ ለፈረንሳይ ኩባንያ በሰጠው የማኔጅመንት ኮንትራት ውል መሠረት የአዲሱ ኮርፖሬሽን ከፍተኛ አመራር ሙሉ በሙሉ በፈረንሳዊያን የተያዘ ሲሆን በሁለተኛና ከዚያ በታች ባሉት እርከኖች ግን ኢትዮጵያዊያን ባለሙያዎች እንደሚመደቡ፤ ከሁለት ዓመት በኋላ አሁን በሁለተኛ ደረጃ የሚገኙት ባለሥልጣኖች የበላይ አመራሩን እንደሚይዙ ተነግሮ ነበር። የማኔጅመንት ኮንትራቱም ዋና ዓላማ ዘመናዊ የቢዝነስ አመራር ልምድን ከፈረንሳዩ ድርጅት ለመቅሰም እንደሆነ ሲወራ ቆይቷል፤ አሁንም ይኸው እየተነገረ ነው። በተግባር እያየነው ያለ ሃቅ ግን ከዚህ እጅግ የተለየ ነው። በትምህርትና በሥራ ልምድ የዳበረ እውቀት ያላቸው በርካታ የቴሌ ባለሙያዎች ተባረዋል፤ ጥቂቶች በዝቅተኛ እርከኖች ተመድበዋል፤ እስካሁን እጣ ፈንታቸውን ያላወቁም አሉ። ከሁለት ዓመት በኋላ ፈረንሳዊያኑን ይተካሉ የተባሉት የሁለተኛው እርከን ሹሞች ደግሞ ቴሌን በማያውቁ ሰላዮችና በወታደሮች ተሞልቷል። የግለሰቦችን የኢሜል አድራሻ ሲለቃቅም የቆየ የመለስ ዜናዊ የሥጋ ዘመድ የሆነ የመንደር “ጆሮ ጠቢ”፣ በቴሌኮሚኒኬሽን ሳይንስ የጠለቀ እውቀት ካለው ባለሙያ የተሻለ የቴሌ ሹመኛ የመሆን እድል አለው። አሁን ባለው ሁኔታ ኢትዮ ቴሌ የስለላ ተቋም እንጂ የሲቪል መሠረተ ልማት ወይም የቢዝነስ ተቋም ነው ማለት አይቻልም። ኢትዮጵያ አገራችን እስካሁን በቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት የዓለም ጭራ መሆኗ ሳያንስ ያላት ደካማ ተቋምም ለስለላ ተግባር መዋሉ የሚያንገበግብ ነው። ቴሌ አቅመ ደካማ እንደሆነ እያወቀ የአገሪቷን የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ካልመራሁ የሚል ትዕቢተኛ ተቋም ነበር፤ አሁን ደግሞ ከድጡ ወደ ማጡ አሽቆልቁሏል።

በኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ መብራትና ኃይል ባለሥልጣንም ተመሳሳይ ነገሮች መታየት ጀምረዋል። የኤሌትሪክ መብራት ኃይል ባለሥልጣን አንዴ በዝናብ እጥረት፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በግድብ መደርመስ፣ አሁን አሁን ደግሞ በመስመሮች የመሸከም አቅም ማነስ እያሳበበ ኢትዮጵያዊያንን በጨለማ ማቆየት የቻለ መሥሪያ ቤት ነው። መብራት ኃይልም እንደ ቴሌ ገበያውን አፍኖ የያዘ፤ በደንበኞቹ መለመን የለመደ፤ ተጠያቂነት የማያውቅ፤ ኃላፊነት የማይሰማው መሥሪያ ቤት ነው። የኤሌክትሪክና መብራት ኃይል ማኔጅመንትም እንደ ቴሌ ሁሉ “የሚሊታራይዜሽን” አደጋ ተጋርጦበታል። ወደፊት የኤሌክትሪክ ኃይል ለጎረቤት አገራት በመሸጥ ጠቀም ያለ ትርፍ ማግኘት ይቻል ይሆናል የሚለው ተስፋ የወያኔ የስለላና ወታደራዊ ተቋማት ዓይን በኤሌክትሪክና መብራት ኃይል ባለሥልጣን ላይ እንዲያርፍ አድርጎታል። የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ባለሥልጣን አመራርም እንደ ቴሌ ሁሉ የሙያው እውቀት በሌላቸው የመለስና አዜብ ዘመዶች በሆኑ ወታደሮችና ሰላዮች በቅርቡ መያዙ አይቀርም።

ሰላዮችና ወታደሮችን በቀጥታ ወደ ከፍተኛ የማኔጅመንት ሥልጣን የማምጣት አሠራር ወደ ብረታ ብረት ኮርፖሬሽ፣ ስኳር ኮርፖሬሽን፣ ቢራ ማምረቻዎች እና ኢትዮጵያ አየር መንገድም እየገባ ነው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ እነዚህም በወታደሮችና ሰላዮች ይመሩ መባሉ የማይቀር ነው። ወያኔ እድሜ ካገኘ ልምዱን ወደሌሎችም ተቋማት ያሸጋግረዋል። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሲቪል ተቋም ይጠፋል፤ ሁሉም ወታደራዊ ይሆናል። ይህ ደግሞ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የተያያዘውን የቁልቁለት ጉዞ ያፈጥናል ብለን እንሰጋለን።

ሁኔታውን በአንክሮ ላጤነ በደርግ ጊዜ እንደነበረው ዓይነት የልማት ተቋማትን በወታደራዊና በስለላ ሹማምንት የመምራት አዝማሚያ ተመልሶ መጥቷል። የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ እንደ ደርግ ሁሉ ሲቪል ተቋማትን ከኢኮኖሚና ማህበራዊ ጠቀሜታቸው ይልቅ ለገዢው ጉጅሌ ወታደራዊ ደህንነት ከሚሰጡት ጥቅም አንፃር ብቻ መቃኘት ጀምሯል። ለማኔጅመት ሥራ የሚያበቁ ባህሪያትም ዘረኝነት፣ ወታደራዊ እውቀትና “ጆሮ-ጠቢነት” ሆነዋል።

ይህ ለምን ሆነ? ለምንስ አሁን ሆነ? ብሎ መጠየቅ ብልህነት ነው። የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ መሠረቱ እየጠበበ መጥቶ ወደ አንድ ወንጀለኛና ባንዳ ቤተሰብ ከገባ ወዲህ ከራሱ ቤተሰብ ውጭ የሚያምነውን ማግኘት ተቸግሯል። ስለሆነም የድርጅቶቹ ሥራ አስኪያጆች የሰላይነትን ሥራ “ደርበው” ለመሥራት ተገደዋል።

በዘረኝነት ላይ ወታደራዊነት ሲታከልበት እጅግ አስከፊ ፋሺስታዊ አገዛዝ ይወጣዋል። በአገራችን እየሆነ ያለው ይኸው ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የትግራይ ገዢ ጉጅሌ በሥልጣን በቆየ መጠን ይበልጥ ዘረኛና ፋሽስታዊ እየሆነ መምጣቱ የማይቀር መሆኑን ደጋግሞ ሲገልጽ የቆየው ከባህርዩ በመነሳት ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## ታዋቂው የእግር ኳስ ተጫዋች መንግስቱ ወርቁ ከዚህ አለም በሞት ተለየ

ተወዳጁ እና ታዋቂው የቀድሞ የኢትዮጵያ ብሔራዊ እግር ኳስ ቡድን ተጫዋች መንግስቱ ወርቁ ከዚህ አለም በሞት መለየቱን ዘገባዎች አመልክተዋል።

በብዙዎች ዘንድ "ታላቁ ኢትዮጵያዊ እግር ኳስ ተጫዋች" በመባል የሚታወቀው መንግስቱ ለሁለት አመታት በባንኮክ ታይላንድ ሲታከም ቆይቶ፤ የመጨረሻ ቀናቱን በእናት አገሩ ለማሳለፍ በመወሰን በቅርቡ ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሰ በ70ኛ አመቱ ማረፉን ኢትዮስፖርትስ የተባለው ድረ-ገጽ ዘግቧል። አቶ መንግስቱ ወርቁ በግል ችሎታው፣ በፍጥነቱ፣ በጉብዝናው እና በሜዳ ላይ በሚያሳየው የራስ መተማመን እንደሚታወቅም ድረ-ገጹ አስታውሷል። አቶ መንግስቱ የብሔራዊ ቡድኑ አሰልጣኝ ሆነው እንዳገለገሉም ለማወቅ ተችሏል።

ለዝግጅት ክፍላችን መልክት ያስተላለፉት የግንቦት 7 ንቅናቄ አመራር አባል አቶ ኤፍሬም ማዴቦ፣ የውድ ተጫዋቹ ስም ለወጣቶች እንግዳ ሊሆን እንደሚችል ጠቅሰው፤ በሳቸው እድሜ ላሉ ኢትዮጵያውያን ግን "መንግስቱ ወርቁ ለእግር ኳስ ማለት ጥላሁን ገሰሰ ለሙዚቃ እንደነበረው ነው" ብለውናል። ሞቱን ሲሰሙ የተሰማቸውን ጥልቅ ሃዘንም ገልጸዋል።

### የወያኔ ጦር ከሰሞኑ በኦጋዴን ንጹሃን ዜጎች . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የጦር ወንጀል መፈጸሙን ይናገራሉ። አገዛዙ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በመቶ ሺሆች የሚቆጠሩ የሶማሌ ክልል ነዋሪዎችን አስገድዶ በማፈናቀል በሌላ አካባቢዎች እያሰፈረ መሆኑን መዘገባችን ይታወሳል።

ዘረኛው ቡድን ከሶስት ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት ለባዳ አገር ነጋዴዎች በርካሽ ዋጋ እየሸጠ በመሆኑ፤ ይህንን ለማሳካት በአገሪቱ ዙሪያ የሚገኙ በመቶ ሺሆች የሚቆጠሩ ገበሬዎችን እና ከብት አርቢዎችን ከቀያቸው እያፈናቀለ ነው። የማፈናቀል ዘመቻውን በስኬት ለማጠናቀቅ ደግሞ ከዚህም የባሰ ከፍተኛ ግፍ ይፈጽማል ተብሎ ይጠበቃል።

### በአለም ዙሪያ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ድርጅቱ ባወጣው በዚህ መግለጫው፥ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ "ሰቆቃ የሞራል ዝቅጠት መገለጫ፣ የአፈና መሳሪያ እና እጅግ ከፉ ከሆኑት የሰብአዊ መብት ረገጣዎች አንዱ ነው" የሚለውን የተባበሩት መንግስታት የጸረ-ሰቆቃ ስምምነት እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ1994 መፈረሙን ጠቅሶ እራሱ በፊርማው ያጸደቀውን አለም አቀፍ ህግ በመተላለፍ በወገኖቻችን ላይ እንዲህ አይነት ዘግናኝ ድብደባ እንዲፈጸም ማድረጉ በወንጀል የሚያስጠይቅ ነው ብሎአል። በስተመጨረሻም ጥምረቱ በኢትዮጵያ ውስጥ እየተካሄዱ ያሉትን የሰቆቃ ተግባራት ለአለም የማሳወቁን ስራ በርትቶ እንደሚሰራ እና ለአለማቀፍ ፍርድ ቤቶች፣ ለሰብአዊ መብት ተሟጋቾች፣ ለለጋሽ አገራት እና ለመሳሰሉት እንደሚያሳውቅ ገልጿል።

ይህንን የንጹሃን ስቃይ የማጋለጥ ስራ የሰሩትን ኢትዮጵያውያን ጀግንነትም አዲሱ ጥምረት አሞግሷል።

### ለጋሽ አገራት በዘረኛው አገዛዝ የእርዳታ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ቡድኑ ግን ለሚፈጸመው ስርቆት ማስረጃ የለም ብሎ መግለጫ ማውጣቱ በተለይም በበርካታ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ንቀትን አትርፎለታል። በመቶዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ገበሬዎች፣ ተማሪዎች፣ መምህራን እና ሌሎችም የመንግስት ሰራተኞች ለሂውማን ራይትስ ዋች በሰጡት ቃለ መጠይቅ፣ ዘረኛው አገዛዝ በነሱ ስም የሚሰበስበውን የእርዳታ ገንዘብ ለፖለቲካ አፈና እያዋለ መሆኑን መመስከራቸው ይታወቃል።

ሂውማን ራይትስ ዋች ሰሞኑን በኢትዮጵያ የአለም ባንክ ተወካይ ለሆኑት ኬን አሃሺ በላከው ግልጽ ደብዳቤ፥ የለጋሾቹ ቡድን እስካሁን በተጋለጠው መረጃ ላይ ምንም ምርመራ አለማካሄዳቸውን አውግዞ፣ ይህ እንዲስተካከል ጥሪ አቅርቧል።



የፖስታሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

## ጀርባህ ካልታጠፈ ማንም ሊሰቀልበት አይችልም

ለጥቁር ህዝብ መብት መከበር እና ለእኩልነት መስፈን ባደረገው ተጋድሎ ከአገሩ አልፎ በአለም ላይ ዝናን ያተረፈው አሜሪካዊው ማርቲን ሉተር ኪንግ ድንቅ ንግግሮች ውስጥ ለጥቅስ ከበቁ በርካታ አባባሎች አንዱ "ጀርባህ ካልታጠፈ ማንም ሊሰቀልበት አይችልም" የሚለው ነው።

ይህንን አባባል ለመተርጎም ሌላ ሁናቴ መጠቀም እንችላለን። ለምሳሌ ሌቦች፥ ባለቤት ካለው ቤት ገብተው አይፈነጩም። በርግጥ፥ የቤቱን ባለቤት ባለን የሃይል ብልጫ ልናንበረክክ እንችላለን ብለው ካልገመቱ በቀር። ጉልበተኛ ነን ባይ ሌቦች ማንን አጥቅተው የሚፈልጉትን ማግኘት እንደሚችሉ ጥናት ሲያካሂዱ፤ ቤተሰቡን እና ንብረቱን በጀግንነት በማስጠበቅ የሚታወቅ ሰው ምንም ያህል የተትረፈረፈ ትርፏት ከቤቱ እንደሚገኝ ቢታመንም አይደፍሩትም ፤ ሊከተል የሚችለውን አደጋ ያውቁታልና ። ስለዚህም ብዙውን ጊዜ የሚመርጡት ደካማ እና እራሱን መከላከል የማይችል ቤተሰብ ነው ብለው የሚያምኑትን ነው።

ይህ ማለት፥ ሰዎች በዚች አለም ላይ ያላቸው የደህንነት ደረጃ፣ መብታቸውን ለማስከበር ካላቸው አቅም ጋር በቀጥታ ይገናኛል ማለት ነው። ይህ አቅም ደግሞ በብዙ መንገዶች የሚገለጥ ሲሆን፣ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ መብቶቹን ለማስጠበቅ አቅምና ችሎታ ያለውን ለይተን እንመልከት። ከኢኮኖሚ ጥቅም አኳያ ሃብትና ንብረቱን ከሌቦች ለመከላከል በቀላሉ የማይሰበር ቁልፍ ያለው ቤት ውስጥ ከሚኖር ሰው ይልቅ አቅመ ብስ ወይም የጎዳና ተዳዳሪ የሆነ ሰው ለማንም ጨካኝ ጉልበተኛ አደጋ የተጋለጠ ነው። በተጓዳኝ መልኩ ለምሳሌ ስለ መብቱ ጠንቅቆ ከሚያውቀው ሰው ይልቅ፣ መብቱ መነካት አለመነካቱን ለይቶ የማያውቀው ለበለጠ አደጋ የተጋለጠ ነው። ስለራሱ ክብር ተቆርቋሪ የሆነና በተፈጥሮ ሊኖረው ሰለሚችለው መብት እውቀት ያለው ሰው ገና ጫፉ ሲነካ ዘሎ መነሳት እና እርምጃ መውሰድ ይችላል። ደካማ ስለሆነኩ መደብደብ እና መረገጥ እጣ ፈንታዬ ነው ብሎ የሚያምነው ደግሞ ተኝቶ ይቀጠቀጣል፤ ንብረቱን ሲቀማ አይኑ እያየ ዝም ይላል። ታዲያ ማርቲን ሉተር ኪንግ "ጀርባህ ካልታጠፈ ማንም ወጥቶ ሊሰቀልበት አይችልም" የሚለን ለዛ ነው።

በመሰረቱ፥ አምባገነኖች እና ጨካኝ አገዛዞች የሚበቅሉት፣ በሆነ መንገድ ጀርባው በታጠፈ ህዝብ ላይ ነው። ግፍና ሲቃይን በስተመጨረሻው የሚያፈራ ዛፍ ፍሬዋ ገና መሬት ላይ ስትወድቅ አይቶ ዝም ያለ ህዝብ ፤ በቅላ እና ነፍስ ስትዘራ፣ ቅጠሎቿም ሲለመልሙ፣ ወይ ባለማወቅ፣ ወይም በ"ምን አገባኝ" ጸጥ ያለ ህዝብ ፤ ጥቂቶች ያቺ ፍሬ በቅላ ካደገች እና ቅርንጫፎቿ ከተንሰራፉ፣ ይዞታዋ እንዲሰፋ ከተፈቀደላት ከቁጥጥር ውጪ ትወጣለች፤ ነገ የራሷን መርዛማ ፍሬዎች እያፈራች አፈሩ ላይ መጣል እና እንደሷ ያሉ ክፉ ዛፎችን ማብዛት ትጀምራለች እና አድጋ ተመንድጋ ከምናለቅስ በእንጭጩ እንንቀላት ብለው ሲጮሁ ሰምቶ ከቁብ ያልቆጠረ ህዝብ፤ ዛፏ በመርዛማ ፍሬዎቿ ሰው ማሳመም፣ መግደል እና አካለ ጎደሉ ማድረግ ስትጀምር እንኳ "እኔ ቤት ጋ እስካልደረሰች ፣ ልጆቼንና ቤተሰቦቼን እስካልጎዳች ምን አገባኝ" የሚል ህዝብ ልብ ሊል የሚገባው አንድ ሃቅ አለ።

ይሄውም ያቺ ዛፍ መርዛማነቷ ለሚበሏት ብቻ ሳይሆን ለአፈሩም፣ ለአየሩም እየሆነ፣ ተጽኖዋ እየተንሰራፋ ይሄዳል። ከአመታት በፊት አንድ እግር ቢጨፈልቃት ያበቃላት የነበረችው ፍሬ፣ አድጋ አና ተመንድጋ የዛፎች እናት ሆና ሰፈር መንደሩን ለማስጠበብ ትበቃለች። ከዛ በኋላ እሷን እና በዙሪያዋ የበቀሉትን መሰል ዛፎች ለማስወገድ የሚፈጀው ጊዜ ብዙ እጥፍ ድርብ ጉልበት እና መስዋእትነት የሚጠይቅ ይሆናል። ጀርባ የማጠፍ መከራው ብዙ ነው።

በኢትዮጵያችን እየሆነ ያለው ከዚህ ምሳሌ ጋር የሚመሳሰል ነው። በተለያዩ ጨቋኝ አምባገነኖች ሥር ፊዳውን ሲቆጥር የኖረ ህዝብ ብሎ ብሎ ዛሬ ከቀደምቶቹ በአላማም በመንፈስም የተለየ ፍጹም ዘረኛና ጎጤኛ በሆነ አገዛዝ ሥር ወድቋል። ይህ የአገራችንን መከራና ሰቆቃ እያራዘመ የሚገኘው ዘረኛ ቡድን በየቀኑ ወንጀል ይፈጽማል። ካለፈው ሳምንት ጀምሮ ለህዝብ ይፋ የሆነው እና በወያኔ እስር ቤቶች ውስጥ በወገኖቻችን ላይ እየተፈጸመ ያለው አሰቃቂ ጥቃት ያጋለጠው መረጃ እንደሚያመለክተው፥ በየቀኑ ከሚፈጽማቸው አሰቃቂ ወንጀሎች ውስጥ አንዱ ንጹሃን ዜጎችን እያፈነ ወደ ሚስጥራዊ እስር ቤቶች በመውሰድ ሰቆቃን መፈጸም ነው። ከነዚህ እስር ቤቶች ውስጥ አንዱ ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ አካባቢ የሚገኘው ነው።

በዚህ የሰቆቃ ጣቢያ ውስጥ በወንድሞቻችን ብልቶች ላይ ውሃ በጠርሙስ እየተንጠለጠለ፤ የዘር ፍሬያቸው እስኪሟሟ እየተደበደቡ፤ በኤሌክትሪክ ሃይል እየተነዘሩ፤ አካለ ጎደሎ እስኪሆኑ ይቀጠቀጣሉ። ሰቆቃውን ለማስቆም ሲሉ ላልሰሩት ወንጀል የሚናዘዙት ማእከላዊ ወደሚባለው ሌላ የሰቆቃ ጣቢያ ይዛወራሉ። እዛ ሲደርሱ፥ ባልሰሩት ወንጀል የተባበሯቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር ደግሞ እስኪወልዱ ድረስ እንደገና ይቀጠቀጣሉ። የሚናዘዙት የጠፉቸው ግን፣ መቼም እንዲህ ካለ ድብደባ በኋላ ቢለቀቁ እና ቤተሰቦቻቸው ቢያዩዋቸው አላስፈላጊ ጥያቄዎች ሊነሱ ስለሚችሉ፤ እዛው ተገድለው ይቀበራሉ።

ጥቁር የመንግስት ኮብራ መኪናዎች ወጣ ገባ ከሚሉበት ከዚህ የሚስጥር እስር ቤት ግቢ ጥቂት ኪሎሜትሮች ራቅ ብሎ የመኖሪያ ቤቶች በመደዳ ቆመዋል። እነዛ ቤቶች ውስጥ ከተለያየ ዘር እና ነገድ የመጡ ኢትዮጵያውያን በመንደራቸው የሚካሄደውን ጉድ ባለማወቅ አገር ሰላም ነው በሚል በማለዳ እየተነሱ ፈጣሪያቸውን በሰላም ስላሳደራቸው ያመሰግናሉ። ቡና ይፈላል፣ ቁርስ ይሰራል፣ ይበላል፣ ይጠጣል፣ ወደ ስራ እና ወደ ትምህርት ቤት ይኬዳል። ማታ እቤት ገብተው በሰላም ያዋላቸውን ፈጣሪ ያመሰግናሉ። እራት በልተው የሰላም እንቅልፍ ያሸልባሉ።

በዛኑ ሰዓት ግን የአንድ ኢትዮጵያዊ እህት፣ የሌላ ኢትዮጵያዊ እናት፣ የሆኑ አዛውንት ብቸኛ ሴት ልጅ ለማታውቀው ወንጀል መክፈል ትጀምራለች። ከሰላማውያኑ ዜጎች ቤቶች ጥቂት ራቅ ብሎ በሚገኘው የምድር ሲኦል ውስጥ፤ የኢትዮጵያዊቷ ሴት ጡቶች በኤሌክትሪክ ሽቦ ይገረፋሉ። እስኪደሙ ይገረፋሉ። ታለቅሳለች። ትጮሃለች። ገራፊዎቿ አንዳንዴ ጩኸቷ ረበሸን እያሉ አፏን በፕላስተር ያሽጉታል። ሌላ ጊዜ ግን መልስ ስለሚፈልጉ፣ ወይም እንደ ሲጋራ የለመዱት የስቃይ ድምጽ ስለሚናፍቃቸው እሽጉን ይፈቱታል። እነሆ! በኢትዮጵያ መንደሮች ውስጥ የተሰገሰጉ የሞት መላእክት፤ የሰው ልክ የማይገባቸው ዘረኞች!

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ! እንዲህ ያለ ወንጀል በመንደርህ የሚፈጸመው፣ በመሰረቱ አንተ ስለፈቀድክ ነው። እነዚህን ወንጀለኞች ዝም ስላልካቸው ነው። ሲበቅሉ ዝም ብለሃል፤ ሲያድጉም ትተሃቸዋምል፤ ሲንሰራፉም ችላ ብለሃል። በርግጥ መርዛማነታቸው ከገባህ ቆይቷል። ይሁን እንጂ እነሱን ቆራርጦ ማገዶ የማድረጉ ስራ ከፍተኛ ዋጋ የሚጠይቅ ሆኖብሃል። ስለዚህም ቀን መቁጠሩን ተያይዘሃል።

እንግዲህ ያለፈው አልፏል። ዝምተኛነት የሚያመጣውን አይተሃል። ዛሬ ግን ሁሉም የሚያበቃበት ቀን ይሁን። ከመንደርህ ጥቂት ራቅ ብሎ ባለ የሰቆቃ ጣቢያ ውስጥ፣ ልጅህ ደራሽ አጥታ እየተሰቃየች መሆኗን አስተውል። ተቆጣ፣ ተናደድ፣ ለመነሳትም ወስን!

### በጋምቤላ የተፈጸመው የዘር ማጥፋት ወንጀል . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

አቶ አባንግ ሜቶ እነ መለስ ዜናዊን ለፈጸሙት ወንጀል ፍርድ ፊት ለማቆም በቂ ህጋዊ መሰረት እና ማስረጃ መኖሩን ጠቅሰዋል። የጋምቤላው ጭፍጨፋ ጉዳይ ብቻ የትግራዩን ገዢ ጉጅሌ ባለስልጣናት ለፍርድ ለማቅረብ ጠንካራ እና በቂ መሆኑን ገልጸው፤ አገዛዙ በሌሎች አካባቢዎች የፈጸመው ወንጀልም ተጨማሪ ጥንካሬ እንደሚሰጠው ተናግረዋል።

አቶ አባንግ፥ በካምቦዲያ ከሃያ አመታት በፊት የተሰበሰበ ማስረጃ በዚህ አመት በወንጀለኞች ላይ እንዳስፈረደ ጠቅሰው፤ እነ መለስ ዜናዊም አንድ ነጥብ ላይ ቀን እንደምትጨልምባቸው እርግጠኛ እንደሆኑ እና ለዛም ተዘጋጅተው እንደሚጠብቋቸው ገልጸዋል።

በርካታ የዘረኛው አገዛዝ ባለስልጣናት በኢትዮጵያ ውስጥ ለፈጸሟቸው የጅምላ ግድያዎች እና ሌሎችም ወንጀሎች በአለማቀፍ ድርጅቶች እና በኢትዮጵያውያን ምርመራ እየተካሄደባቸው እንደሆነ ከዚህ ቀደም ዘግበናል።

### የወያኔ "ባለስልጣናት ሆዳቸው አይሞላም" ሲል . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ቤቶች አይመስሉም። አንድ ውስጥ አዋቂ ምንጭ ጉዳዩን ሲያብራሩ፥ ሁሉም ነገር የሚሰራው በመመሳጠር በመሆኑ ዛሬ አንድ ከንቲባ ቢሮ መግባት ላይ ካለ ሚኒስቴር ጋር ቀጥታ እንደመገናኘት ነው።

እኚሁ ግለሰብ እንደሚሉት፥ የመንግስት መስሪያ ቤቶች "ለአንዳንዱ እንደ እናቱ ቤት፣ ለሌላው እንደ እንጀራ እናት ቤት ሆነዋል"። ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ውስጥ በአንድ ግለሰብ እጅ 30 የመሬት ካርታዎች መያዛቸውን የገለጹት ምንጫችን፤ በርካታ ህግ ተከትለው መሬት የጠየቁና፣ ይሰጣችኋል ተብለው ደረሰኝ የተቀበሉ ግለሰቦች ግን አንዲት ቤት መስሪያ መሬት ለመረከብ አራት አምስት አመታት ይንከራተታሉ ብለዋል።

የዘረኛው አገዛዝ ባለስልጣናት በሙስናው ውስጥ እጃቸው እያለበት ህገ-ወጥ የመሬት ንግድን በመዋጋት ስም በሰበታ ከተማ ላይ ትኩረታቸውን መጣላቸው ያልገባው ከንቲባም፤ ለባለስልጣናቱ ሁሉ የሚፈልጉትን ያህል መሬት ማደሉን ጠቅሶ፣ "ሰው ጠገብኩ አያውቅም" ሲል ተደምጧል። አዜብ መስፍን በሺሆች የሚቆጠር ካሬ ሜትር መሬት በሰበታ እንዳላት ከዚህ ቀደም መዘገባችን ይታወሳል።

የከተማይቱን ሰራተኞች መታሰር ተከትሎ ከንቲባው ከስልጣኑ እንደወረደ የታወቀ ሲሆን፤ ይህ ግን ህዝብን ለማታለል እንደሆነ እና ግለሰቡ ወደ ሌላ መስሪያ ቤት ተወስዶ ምክትል ሃላፊ ሆኖ መሾሙን ምንጫችን ገልጸዋል።

## የኦሮምያ ክልል መንግስት ለሰራተኞቹ ደሞዝ በጊዜ መክፈል እየተሳነው ነው ተባለ

በቂ ጥናት ሳይደረግባቸው ለፕሮፓጋንዳ እና ለዘረፋ እንዲመቹ ብቻ እየተካሄዱ ያሉ ፕሮጀክቶች የህዝብን ሃብት ለብክነት፣ እና ዜጎችን ለእንግልት እየዳረጉ ሲሆን፤ የኦሮምያ ክልል መንግስትንም እያዳከሙት ነው ስትል የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከአዲስ አበባ ባስተላለፈችው ዘገባ ገልጻለች።

በአዳማ ከተማ የአባ ገዳ የስብሰባ አዳራሽ በአስርት የሚቆጠሩ የክልሉ የቢሮ ሃላፊዎች በተገኙበት ያለፉትን አምስት አመታት ሂደት የሚገመግም ስብሰባ እንደተካሄደ የገለጸችው ዘጋቢያችን፤ ከስብሰባው መሪዎች አንዱ ያለፈው የአምስት አመት እቅዳችን ምንም ፋይዳ አልነበረውም ብሎ ሲናገር መደመጡን እና ይህም ከተካፋዮቹ አንዱ የነበሩትን ምንጯን እንዳስገረመ ትናገራለች።

የዛሬ አምስት አመት በተካሄደው ስብሰባ ላይም መገኘታቸውን የሚገልጹት ግለሰብ፤ ዛሬ እቅዱ ምንም ፋይዳ እንደሌለው የሚናገሩት የክልሉ ባለስልጣናት፣ የዛሬ አምስት አመት የበላይ አዛዦቻቸው ሰው ሳያማክሩ በዘፈቀደ ፈጥረው የሰጧቸውን እቅድ ካላስፈጸማችሁ ብለው ያስገደዱን ናቸው ብለዋል። በክልሉ ውስጥ በቂ ጥናት ሳይካሄድባቸው በካቢኔው የዘፈቀደ ትእዛዝ ብቻ እየተካሄዱ ያሉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ፕሮጀክቶች እንዳሉ የታወቀ ሲሆን፤ አንዳንዶቹ ፕሮጀክቶች ከተፈጸሙ በኋላ አስቀድሞ ያልተገመተ ችግር በመፈጠሩ ከስራ ውጪ እንደሚሆኑ ለማወቅ ችለናል።

የክልሉን የገንዘብ አቅም ሳያገናዝቡ በየአቅጣጫው የተጀመሩት ስራዎችም የበጀት ጫና መፍጠር ጀምረዋል። እንደ ዘጋቢያችን ገለጻ፣ በአሁኑ ሰአት በክልሉ ከተሞች የሚሰሩ መምህራን እና ሌሎች የመንግስት ሰራተኞች ደሞዛቸውን በጊዜ አያገኙም። ለህዝብ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተመለከተ፣ ለምሳሌ የቢሾፍቱ ከተማ ህዝብ የቧንቧ ውሃ ካገኘ አራት ወር ሊሆነው እንደሆነ ታውቋል።

የዘጋቢያችን ምንጭ፥ የክልሉን ቢሮዎች የስራ ሂደት ለማሻሻል በሚል ስም በስራ ላይ ውሎ አሁን ምንም ፋይዳ እንዳላስገኘ በሚነገርለት ቢ.ፒ.አር. ላይ ብቻ የባከነው ገንዘብ ለደሃው ህዝብ ሶስት ደረጃቸውን የጠበቁ ሆስፒታሎች ይገነባ ነበር ብለዋል።

## የመሬት ቅሚያው የአንዳንድ ብሔረሰቦችን የአኗኗር ዘይቤ አደጋ ላይ ጥሏል ተባለ

የእንግሊዙ "ብሪቲሽ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን" ወይም ቢቢሲ ሰሞኑን አጠናቅሮ ባወጣው ሰፊ ዘገባ፤ በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለው የመሬት ቅሚያ የአንዳንድ ብሔረሰቦችን የአኗኗር ዘይቤ አደጋ ላይ መጣሉን አትቷል።

ቢቢሲ፥ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ተቃውሞ በማሰማታችን ተጠቅተናል የሚሉ ዜጎችንም ቃለ መጠይቅ አድርጓል። አንድ ስሙ እንዳይገለጽ የፈለገ የጋምቤላ ነዋሪም፥ "ስለ መሬት ጉዳይ አሁን በነፃነት መናገር አትችልም፤ ልትታሰር እና ልትገደል ትችላለህ፤ ይህ በደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ለሚኖሩ ብሔረሰቦች ሁሉ የጨለማ ዘመን ነው" ብሏል።

የትግራዩ ገገር ጉጅሌ 3 ሚሊዮን ሄክታር ወይም ቤልጂየምን የሚያክል መሬት ለባዳ አገር ነጋዴዎች የማደል እቅድ ይዞ ተነስቶ፤ ለዚህም ይሆን ዘንድ በርካታ መንደሮችን እየነቀለ እና ዜጎችን እያፈናቀለ መሆኑን ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ ዘግበናል። በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ይህንን ተግባሩን እንዳጠናከረ እና በመቶ ሺሆች የሚቆጠሩ የጠረፋማ ክልሎች ነዋሪዎችን በግዳጅ እያፈናቀለ መሆኑንም መዘገባችን ይታወሳል።

አገዛዙ እያደልኩ ያለሁት መሬት ማንም የማይጠቀምበትን ነው ማለቱን የጠቀሰው ቢቢሲ፤ የአካባቢው ነዋሪዎች ሲጠየቁ ግን አብዛኞቹ የሚተዳደሩት በከብት እርባታ ስለሆነ በየወቅቱ ከወዲያ ወዲህ በመዘዋወር ስለሚኖሩ የማይጠቀም መሬት ብሎ ነገር እንደሌለ መናገራቸውን ዘግቧል። አንድ ነዋሪም፥ "መሬት የምንጠቀመው ለተለያዩ ጉዳዮች ነው - ለእርሻ፣ ለአደን እና በረሃብ ወቅት እየተዘዋወርን ፍራፍሬ ለመልቀም" ብሏል። "ጋምቤላ ውስጥ ባዶ መሬት ብሎ ነገር የለም። መንደሮች ተነቅለዋል፤ መንደርተኞቹም መሬታቸውን እንዲሸጡ ጉቦ ተሰጥቷቸዋል። መሬቱን ግን ሊሸጡት አይችሉም፤ የነሱ አይደለም። መሬቱ የአያቶቻችን ነው።" ሲልም ጨምሯል።

አንዳንድ የአካባቢው ገበሬዎች የተወሰነ ካሳ ቢሰጣቸውም፤ ከብት አርቢዎች ግን ምንም እንዳልተቀበሉም ዘገባው አመልክቷል። የጋምቤላ ነዋሪዎች ይህ የባህላቸው መጥፊያ ነው ብለው እንደሚያምኑ ለቢቢሲ ተናግረዋል። የትግራዩ ገገር ጉጅሌ ይህንን ፖሊሲ በአፋር እና በሶማሌ ክልልም እየፈጸመ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፤ አበራ ዴሬሳ የተባለ አንድ ሹመኛ፥ የከብት አርቢዎች አኗኗር ለእድገት ምቹ ስላልሆነ አገዛዙ ያንን ማጥፋት እንደሚፈልግ በግልጽ ተናግሯል።

## በመንግስት ሰራተኞች ቅጥር ላይ እገዳ እየተደረገ ነው

ከግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት በፊት ድጋፍ ለማግኘት ሲል ገገርውን ቡድን ለተቀላቀሉ ሁሉ ስራ እሰጣለሁ እያለ አባላትን በጥቅም ሲያግበሰብስ የቆየው የወያኔ አገዛዝ የቅጥር እገዳ መጀመሩን ለማወቅ ተችሎአል።

የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከአዲስ አበባ ባስተላለፈችው ዘገባ፥ የኦሮምያ ክልል አስቸኳይ የቅጥር እገዳ ትእዛዝ በማስተላለፍ ይህንን በስራ ላይ አውሏል። በቅርቡ አንድ የክልሉ ምክትል ፕሬዚደንት ቢሮ ሹመኛ የአስተዳደር እና የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ ሃላፊዎችን ሰብስቦ፤ አገዛዙ ለሚቀጥሉት አምስት አመታት ያወጣውን እቅድ በተገቢው መንገድ ለማስኬድ አንዳንድ ማስተካከያዎች እንደሚደረጉ በማስታወቅ፤ እስከዛ ድረስ ሃላፊዎቹ ላልተወሰነ ጊዜ ቅጥር እንዲያቆሙ ትእዛዝ አስተላልፏል። ይህንንም ትእዛዝ የያዘ ሰርኩላር ለየቢሮዎቹ ተላልፏል።

የኦሮምያ ክልል ምንጮች ለዘጋቢያችን እንደተናገሩት፥ አዲሱ የቅጥር እገዳ የአገዛዙን የውሸት ተስፋ ተቀብለው በየቢሮው ስራ ፍለጋ የሚኳትኑትን አዳዲስ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምሩቃን ክፉኛ ይጎዳል። "አገዛዙ በአገሪቱ ውስጥ የተማረ የሰው ሃይል እጥረት አለ እያለ ዘወትር ያላዝናል" ያሉን ምንጭ፤ "አሁን ስራ አጥቶ የሚንከራተተው ባለ ዲግሪ እና ዲፕሎማው ነው" ብለዋል። "የአገሪቱ ኢኮኖሚ እንዳው እንደዚህ እያደገ እና እየሰፋ ነው ከተባለ፤ ለነዚህ ወጣቶች እየተፈጠረ ያለው ስራ የታለ?" ሲሉም ጠይቀዋል።

ግለሰቡ ጨምረው፥ የቅጥር እገዳው ቋሚ ሰራተኞችንም ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ መክተቱን ገልጸዋል። ሰራተኞች በየጊዜው ለገዛ ስራቸው እንደ አዲስ እንዲወዳደሩ እየተደረጉ እና እየተባረሩ ስላሉ ሰው ሁሉ በጭንቅ ውስጥ እንደሚኖር አስረድተዋል።

በኦሮምያ ክልል ቢሮዎች ውስጥ ለትግራዩ ገገር ጉጅሌ ያለው ጥላቻ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መሆኑን ዘጋቢያችን ገልጻለች።

## የአዲስ አበባ ኮንዶሚኒየም ነዋሪዎች ውሃ እያገኘን አይደለም አሉ

በአዲስ አበባ ኮንዶሚኒየሞች ውስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን አስፈላጊ አገልግሎቶችን እያገኘን አይደለም ሲሉ ለግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ምሬታቸውን ገልጸዋል።

የወያኔ አገዛዝ የመንግስትን አቅም ከግምት ሳያስገባ እና ያለ በቂ ጥናት፣ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ እና ለካድሬዎቹ የሙስና እድል ለመፍጠር ሲል ሰፊ ግንባታዎችን እንደሚያካሂድ እና አዳዲስ ፕሮጀክቶችን እንደሚጀምር ይታወቃል። እነዚህ ፕሮጀክቶችም ወይ አገልግሎት ያልተሟላላቸው፣ ወይም ጭራሽ ተጠቃሚ የማያገኙ ሲሆኑ ተስተውሏል። ለምሳሌ በተለያዩ የክፍላተ ሃገራት ከተሞች ያለ በቂ ጥናት የተገነቡ በርካታ የኮንዶሚኒየም ህንጻዎች ገገር አጥተው የከብቶች እና የአህያዎች ማደሪያ መሆናቸውን ከዚህ ቀደም መዘገባችን ይታወሳል።

የተጠቃሚዎች እጥረት በሌለባት አዲስ አበባ ደግሞ በርካቶች ኮንዶሚኒየም እንደሚያገኙ ቃል ተገብቶላቸው እና መነሻ ክፍያ ከፍለው ለአመታት እየጠበቁ ሲሆን፤ እድል ደርሷቸው ያገኙት በአገልግሎት እጥረት እየተንገላቱ ነው። ሰሞኑን ዘጋቢያችንን ያናገሩት አንድ የኮንዶሚኒየም ነዋሪ፥ የውሃ አገልግሎት በሁለት ሳምንት አንዴ እንደሚደርሳቸው ገልጸው፣ "የመብራት እንኳ አይነገር" ብለዋል። የኮንዶሚኒየም ህንጻዎች ደግሞ ዘመናዊ ተብዬ በመሆናቸው መጸዳጃ እና ማእድ ቤቶቻቸው በአግባቡ እንዲሰሩ እነዚህ አገልግሎቶች እጅግ አስፈላጊ ናቸው።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እስከ 3:30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2:30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org